ሰኔ 2 ቀን 2021 ዓ.ም.

Washington Grove Elementary School

የተወደዳችሁ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ተማሪዎች፣ እና የሥራ ባልደረቦች፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመጠጥ ውኃ ምርመራ ፕሮግራም አካል በመሆኑ፣ የእርስዎ ትምህርት ቤት ምርመራ የተጠናቀቀ ሲሆን በ "Montgomery County Council Action Level (AL) of 5 parts per billion (ppb)" ከተገለጸው በላይ በአንድ ወይም በይበልጥ የውኃ ማስተላለፊያዎች ላይ በብዛት የሌድ ክምችት (lead concentrations) ተገኝቷል። ዝርዝር ዘገባዉ በ MCPS የመጠጥ ውሃ ምርመራ ፕሮግራም ድረገጽ ላይ ይገኛል፡-

[http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/facilities/maintenance/services/water.aspx](http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/facilities/maintenance/services/water.aspx)።

የሜሪላንድ የአካባቢ ጥበቃ (MDE) ደንቦችን በመከተል ፣ ከፍ ያለ የሊድ/እርሳስ ክምችት የያዙ ማስተላለፊያዎች/ማውጫዎች ከአገልግሎት ተወግደዋል እናም ለእነዚህ ማስተላለፊያዎች/ማውጫዎች የማሻሻያ/የመፍትሄ እቅድ ይተገበራል። ማሻሻያ/የመፍትሔ እርምጃ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የተወሰዱት እርምጃዎች ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በማስተላለፊያዎች/ማውጫዎች ላይ ዳግም ፍተሻ/ምርመራ ይደረጋል።

የመጠጥ ዉሃ ማስተላለፊያዎች/ማውጫዎች ፍተሻ/ምርመራ በየሶስት ዓመት ዑደት ይከናወናሉ።

## ሊድ/እርሳስ በጤና ላይ ያለዉ ተጽእኖዎች/ውጤቶች

ውሃ ከመጠጣት ወይም ከሌሎች ምንጮች ከመጠን በላይ ሊድ/እርሳስ ሰውነትዎ ውስጥ ከገባ ከባድ የጤና ችግሮች ሊያስከትል ይችላል። በአንጎል እና በኩላሊት ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፣ እንዲሁም ኦክስጅንን ወደ ሁሉም የሰውነት ክፍሎች የሚያደርሱትን የቀይ የደም ሴሎች ማምረት ላይ ጣልቃ ሊገባ ይችላል። ለሊድ/እርሳስ ተጋላጭነት ትልቁ አደጋ በጨቅላ ሕፃናት ፣ ታዳጊ ሕፃናት፣ እና በእርጉዝ ሴቶች ላይ ነው። ሊድ/እርሳስ በአጥንቶች ውስጥ ይከማቻል እናም ከእድሜ ቆይታ በኋላ ሊወጣ ይችላል። በእርግዝና ወቅት፣ ፅንሱ የአንጎል እድገትን ሊጎዳ የሚችለውን ሊድ/እርሳስ ፣ ከእናት አጥንቶች ውስጥ ይቀበላል/ያገኛል። የሳይንስ ሊቆች በአንጎል ላይ የሊድ/እርሳስ ተጽእኖዎችን/ውጤቶችን ከልጆች ዝቅ ያለ IQ ጋር አገናኝተዉታል። የኩላሊት ችግር እና ከፍተኛ የደም ግፊት ያለባቸዉ አዋቂዎች ከጤነኛ አዋቂዎች ይበልጥ በዝቅተኛ ደረጃዎች ሊድ/እርሳስ ሊጎዱ ይችላሉ።

## የሰብአዊ ፍጡር ለሊድ/እርሳስ መጋለጫ ምንጮች

የሰብአዊ ፍጡር ለሊድ/እርሳስ መጋለጫ በርካታ የተለያዩ ምንጮች አሉ። እነዚህም የሚያካትቱት፡- ሊድን/እርሳስን መሰረት ያደረገ ቀለም፣በሊድ/እርሳስ የተበከለ አቧራ ወይም አፈር ፣አንዳንድ የቧንቧ እቃዎች፣የተወሰኑ የሸክላ ዓይነቶች፣ከሊድ/እርሳስ እና ቆርቆሮ ድብልቅ የተሰሩ ነገሮች፣የነሐስ የቤት እቃዎች/መገልገያዎች፣ምግብ፣ እና መዋቢያዎች፣ በሥራ ቦታ እና አንዳንድ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያዎች ተጋላጭነት ናቸዉ። በ Environmental Protection Agency (EPA)/በአካባቢ ጥበቃ ኤጄንሲ መሰረት፣የአንድ ሰው ለሊድ/እርሳስ የመጋለጥ እድሉ/ሏ ከ 10 እስከ 20 በመቶ የሚሆነው ከመጠጥ ውሃ ሊመጣ የሚችል ሲሆን፣ ሊድ/እርሳስ ባለዉ ውሃ የተደባለቀ ፎርሙላ/ወተት ለሚመገብ/ለምትመገብ ጨቅላ ሕፃን ደግሞ ይህ ከ 40 እስከ 60 በመቶ ሊጨምር ይችላል።

## በመጠጥ ዉሃ ዉስጥ የሊድ/እርሳስ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ፡-

1. ሊዱን/እርሳሱን ለማስወጣት ውሃዉ እንዲፈስ ያድርጉ፡- ውሃው ለብዙ ሰዓታት አገልግሎት ላይ ያልዋለ ከሆነ ፣ ለመጠጥ ወይም ምግብ ለማብሰል ከመጠቀምዎ በፊት፣ ቋሚ የሙቀት መጠን/ተምፕሬቸር ላይ እስኪደርስ ድረስ ወይም እስኪቀዘቅዝ ድረስ ከ 15 እስከ 30 ሰከንዶች ያህል ውሃው እንዲፈስ ያድርጉ።
2. የሕፃናትን ፎርሙላ/ምግብ ለማዘጋጀት እና ለማብሰል ቀዝቃዛ ውሃ ይጠቀሙ፡- ከቧንቧው የሚወጣው ሊድ/እርሳስ በቀላሉ ወደ ሙቅ ውሃ ይቀልጣል/ይሟሟል።

*እባክዎን ያስታውሱ ውሃን ማፍላት የሊድ/እርሳስን መጠን አይቀንሰውም።*

## ተጨማሪ መረጃ

በቤትዎ/ህንፃዎ ዙሪያ ለሊድ/ለእርሳስ መጋለጥን ለመቀነስ እና ስለ ሊድ/እርሳስ የጤና ተፅእኖዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ፣የ EPA ን ድረጣቢያ ይጎብኙ በ www.epa.gov/lead። ለሊድ/እርሳስ ስለ መጋለጥ የሚያሳስብዎት ነገር ካለ፣ ልጅዎ እንዴት እንደሚመረምር/እንደምትመረመር ለማወቅ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

ማንኛዉም አይነት ጥያቄ ቢኖርዎት፣ እባክዎን የአካባቢ ቡድን መሪ Brian Mullikin ን በ 240.740.2324 ወይም በ brian_a_mullikin@mcpsmd.org ያግኙ።

ከአክብሮት ጋር ፣

Lynne Zárate, Director/ዳይሬክተር
Division of Sustainability and Compliance